ITU መመሪያዎች

ዲጂታል መረጃ፣ አገልግሎቶች እና ምርቶች በ COVID-19 ግዜ አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ፣ ለሁሉም ሰዎች አንዴት ተደራሽ ማድረግ እንደሚቻል ማረጋገጥን በተመለከተ።[i]

አለም ከዚ በፊት አይታው በማታቀው መልኩ ICT(Information and Communication Technologies) ብቸኛው በሚባል ደረጃ ለሰዎች አርስ በርስ መገናኛ ዕድል ሆኗል። የሰው ልጅ ከዚ በፊት በሂዎት ለመቆየት ሚያስፈልጉትን መረጃዎችን ወይም ዋና ዋና አገልግሎቶችን አና ምርቶችን ለማግኘት አንዲ አይነት የ ዲጂታል ጥገኝነት አይቶ አያቅም። ስለሆነም፣ በ COVID-19 ወረርሺኝ ግዜ መረጃን አና መመሪያዎችን ማግኘት ጾታን፣ ብቃትን፣ አድሜን ወይም ቦታን ሳይለይ ለሁሉም ህብረተሰብ በጣም ወሳኝ ነው።

በዚህም ምክንያት፣ በ COVID-19 ዙሪያ ቁልፍ የሆኑ ዲጂታል መረጃዎች ተደራሽ በሆነ መልኩ መሰራጨታቸው አና መገኘት መቻላቸው አስፈላጊ ነው፣ ሁሉም ህብረተሰብ ጋር እንደሚደርስ ለማረጋገጥ እናም ማንም ሰው ወደሁዋላ እንዳይቀር፣ በተለይ የማየት እና መስማት ችግር ላለባቸው እንደ እስክሪን ማንበብያ(Screan Reader) ፣ መግለጫ ጽሁፍ ወይም የምልክት ቋንቋ አንብበው እንዲረዱ ዲጂታል መረጃዎችን በተጨማሪ መፍቴዎችን ሚፈልጉ። ያለዚያ፣ በርካታ አካል ጉዳተኞች በዚ ወረርሽ ግዜ ሊወሰዱ አና ሊከበሩ የሚገቡ ጥንቃቄዎች እና እርምጃዎች መረጃ እጥረት ሳቢያ ከፍተኛ ለሆነ ብክለት ይጋለጣሉ።[1]

ስለሆነም, በቀላል ቋንቋ መረጃን ከማቅረብ፣ ለማንበብ ቀላል ከሆኑት እና ተደራሽ በሆኑ ቅርፀቶችን ከማቅረብ በተጨማሪ እንደ ተደራሽ ድርጣቢያዎች፣ ስልክ፣ ሬዲዮ፣ ቪዲዮ፣ በራሪ ጽሑፍ፣ መግለጫ ጽሑፍ፣ ቻት ወዘተ ያሉ በርካታ የግንኙነት አውታሮችን መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የህዝብ ጤና መረጃ ተደራሽ መሆኑን ለማረጋገጥ (ለ መስማት ለተሳናቸው እና መስማት ለሚከብዳቸው ሰዎች አገልግሎቶችን ጨምሮ) የተስተካከሉ የእርዳታ መስመሮችን እና ግንዛቤ ማግኘት የዓለም አቀፍ ወረርሽኝ መስፋፋት እና ተፅእኖን ለመቀነስ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ብዙ የአካል ጉዳተኞች እንደ መድሃኒቶች፣ የንጽህና ምርቶች እና ምግብ የመሳሰሉ ጤናቸውን ለመጠበቅ አስፈላጊ ነገሮች በመደበኛነት ቤታቸው በሚቀርብላቸው ለይ ጥገኛ ናቸው፡፡ ስለሆነም፣ ከማስታወቂያዎች ተጽኖ በማህበራዊ እርቀት እና በአነስተና መረዳጃ አውታሮች ለይ በተጨማሪ ቸርቻሪዎች እንዲሁም የጤና አጠባበቅ ምርቶች እና አገልግሎት ሰጭዎች እና ሌሎች ቁልፍ ድርጅቶች የመስመር ላይ (online) መረጃዎቻቸውን፣ አገልግሎቶቻቸውን እና ምርቶቻቸውን ተደራሽነት የማያረጋግጡ ከሆነ ብዙ የአካል ጉዳተኞች አስፈላጊ መረጃ፣ የመድኃኒት እና በሌሎች ወሳኝ ምርቶች እና አገልግሎቶች እጥረት መከኒያት ህይወታቸው ለአደጋ ተጋላጭ ሊሆን ይችላል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በ COVID-19 ወረርሽኝ ውስጥ የICT ዋና ሚና ከተሰጠ በኋላ ቁልፍ መልዕክቶችን እና እርምጃዎችን የያዙ የሚከተሉት መመሪያዎች ዲጂታል መረጃ፣ አገልግሎቶች እና ምርቶች በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ አካል ጉዳተኞችንም ጨምሮ ለሁሉም ሰዎች ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የተሰጡ ናቸው፣ እንዲሁም በዚህ ዓለም አቀፍ አስቸጋሪ ቀውስ ውስጥ ማንም ወደኋላ እንዳይቀር።

---

[1] ITU የቪዲዮ ስልጠናዎች ዲጂታል ይዘትን እንዴት ማጎልበት እና ማረም እንደሚቻል ላይ

IT-D በእራስ ፍጥነት የሚሄድ ነጻ የዖንላይን ስልጠና በ ICT ተደራሽነት ዙሪያ በሚከተሉት አድራሻዎች

- *የ ICT ተደራሽነት - ለ ሁሉን አቀፍ ግንኙነት ቁልፍ*
- *የድር ገጽ ተደራሽነት - የአካታች ዲጂታል ማህበረሰብ የማዕዘን ድንጋይ*

ቁልፍ መልእክቶች እና ተግባራት

1. **የአካል ጉዳተኛ ሰዎችን ጨምሮ ሁሉንም ሰዎች አስፈላጊ የሆነውን ይህን መረጃ ማግኘት እንዲችሉ የ COVID-19 ን ብክለትን ለመቀነስ ቁልፍ ዲጂታል መረጃ፣ አገልግሎቶች እና መሰፈርቶች በተደራሽ ቅርፀቶች መኖራቸውን ያረጋግጡ፡፡**

አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ በሁሉም ሰው ዘንድ COVID-19 ን በተመለከተ የሚቀርቡ ይዘቶች እንዲሁም መረጃዎች ተደራሽ በሆነ ቅርፀቶች መቅረብ አለበት፡፡ ለምሳሌ፣ የህዝብ የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች፣ የመስመር ላይ(online) ቪዲዮዎች እና በድምጽ ብቻ የተመሰረቱ የድር ገጽ ስርጭቶች ንዑስ ርዕሶችን(subtitles) ወይም የምልክት ቋንቋ ትርጉም እስካልተካተተባቸው ድረስ መስማት ለተሳናቸው ሰዎች ተደራሽ አያደርጋቸውም። እንደማንኛውም ሌላ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ከባህላዊ ሚዲያ መንገዶች(ቴሌቪዥንና ሬዲዮ) በስተቀር የICT ዓለም በእንደዚህ ያሉ ያልተለመዱ ሁኔታዎች ውስጥ ለአካል ጉዳተኞች ግንኙነትን የሚያመቻቹ የተለያዩ አሠራሮችን ያቀፈ ነው፥ መደበኛ ስልክ፣ የሞባይል ድምጽ ፣ SMS/የጽሑፍ መልእክቶች አንዲሁም በይነመረብ አገልግሎቶች እና ሃድቶች እንደ ድር ጣቢያዎች፣ ቪዲዮ፣ ፈጣን የመልእክት መላላኪያ መተግበሪያዎች፣ የበይነመረብ ፕሮቶኮል (IP) ያሉ የድምጽ አገልግሎቶች እና ፈጣን ግኑኝነትን እና ዲጂታል ይዘት ያላቸው (ምስሎች ፣ ቪዲዮዎች እና ሰነዶች) መላላክ ሚፈቅዱ የድር አገልግሎት ኮንፈረንስን መሠረት ያደረጉ ማህበራዊ ድህረ ገጾች እና የሳተላይት ግንኙነቶች፡፡

2. **የአካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ሁሉም ሰዎች ዲጂታል መረጃዎችን እና አገልግሎቶችን ማግኘት፣ መረዳትና መጠቀም መቻላቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ገጽታዎች ከግምት መግባት አለባቸው፡፡**

   a. **የህዝብ መረጃ፥** እንደ የባቡር ጣቢያዎች፣ የቸርቻሮ መደብሮች፣ መናፈሻዎች እና ሌሎች የሕዝባዊ ቦታዎች በኤሌክትሮኒክ ማሳያ ገጾች በኩል በድምጽ እና በምስል ቅርፀቶች በኩል የሚቀርቡ የህዝብ መረጃዎች የግል የICT መሳሪያዎች ማግኘት ለማይችሉ ሰዎች ተደራሽ ይሆናል፡፡ ከተቻለ፣ ግራፊክስ እና ምስሎች ከጽሑፍ በተጨማሪ መታየት አለባቸው። በአደጋ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ ማንቂያ ድምጾች እና/ወይም ሳይረኖች የአስጊነቱን ሁኔታ እና ደረጃን ለማመልከት ሚበሩና ሚጠፉ መብራቶችን ማካተት አለባቸው። በሕዝባዊ አድራሻ ስርዓቶች በኩል የሚቀርቡ መረጃዎች እና ማሳሰቢያዎች እንዲሁ በሚታዩ ዲጂታል አማራጮች አማካይነት መቅረብ አለባቸው።[2][3][4]

   b. **ሬዲዮን** ከአባሪ ጋር ወይም ልዩ ከሆኑ ነገሮች ጋር መስማት ለተሳናቸው ወይም መስማት ለሚከብዳቸው ሰዎች መጠቀሚያ መሆን ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ መስማት ለተሳናቸው እና መስማት ለሚከብዳቸው ግለሰቦች እንዲነቁ በመንግስት በኩል COVID-19'ን ተያይዞ የሚወጡ ገደቦችን ብክለትን ለመገደብ የሚያስችሉ ስርጭቶችን እንደ ቫይብሬሽን፣ ሚበሩና ሚጠፉ መብራቶች እና ቀላል ጽሑፎች መቀየር የሚችሉ መሳርያዎች። የመስመር(online) ላይ ሬዲዮ በቀጥታ ወይም ፖድካስቶች ይዘቱን በ ጽሁፍ ማካተት አለባቸው፡፡[5]

   c. **ቴሌቪዥን:** ቋንቋውን የመረዳት ችግር ወይም የመስማት ችግር ላለባቸው ሰዎች የ COVID-19 ጋር የተዛመዱ የኦዲዮ ሐተታዎች ለይ በአከባቢው ቋንቋ መግለጫ ፅሁፍ/ንዑስ-ጽሑፍ መካተት አለበት፡፡ በተጨማሪም ስለ ወረርሽኙ ሁኔታ የቴሌቪዥን መረጃ በሚሰጥበት ጊዜ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፡፡[6]

---

[2] * የትራንስፖርት ክፍል እና ክፍለ ስኮትላንድ። ተደራሽ ለሆኑ የባቡር ጣቢያዎች ዲዛይን ደረጃዎች - የተግባር ልምምድ ሕግ ፣ ገጽ 109 ፣ K7 ምልክቶች-ማሳያ እስክሪኖች.

[3] * የUS መዳረሻ ቦርድ፡፡ 702 የአደጋ ጊዜ ደወል ስርዓቶች

[4] * የትራንስፖርት ክፍል እና ክፍለ ስኮትላንድ። ተደራሽ ለሆኑ የባቡር ጣቢያዎች ዲዛይን ደረጃዎች - የተግባር ልምምድ ሕግ ፣ ገጽ 115 ፣ L1። ማስታወቂያዎች - አጠቃላይ፡፡

[5]*ብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች ምክር ቤት በ "ለአካል ጉዳተኞች ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ (ግንኙነቶች)፥ ከ ድንገተኛው በፊት ፣ ወቅት እና በኋላ።" ገጽ 45፥ የተደራሽነት መፍትሔዎች ፤ ገጽ 104 ሠንጠረዥ 9. ማንቂያዎችን የማቀበል እና የማረጋገጥ ዘዴዎች፤ ገጽ 148 እያደገ ሚሄድ ልምምድ ፥በ መስል የተደገፈ ሬዲዮ

[6] ብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች ምክር ቤት በ "ለአካል ጉዳተኞች ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ (ግንኙነቶች)፥ ከ ድንገተኛው በፊት ፣ ወቅት እና በኋላ"፡፡ ገጽ 45፥ የተደራሽነት መፍትሔዎች ፤ ገጽ 104 ሠንጠረዥ 9. ማንቂያዎችን የማቀበል እና የማረጋገጥ ዘዴዎች፤

d. **SMS:** መረጃ እንደ SMS ብቻ ሚላክ ከሆነ፣ እይታ አልባ(non-visual) ግብዓት የሚፈልጉ እና ጽሁፍን ወደ ድምጽ የሚቀይሩ ከፍ ያሉ መሳሪያዎችን ማግኘት የማይችሉ ሳይካተቱ ይቀራሉ። ስለሆነም ከ COVID-19 ወረርሽኝ ጋር የተዛመዱ እርምጃዎችን በተመለከተ ማስጠንቀቂያዎች እንዲሁም ማንቂያዎች በተለያዩ የሥርጭት ጣቢያዎች ላይ በበርካታ ቅርጾች ሊወጡ ይገባል፡፡ ከመልዕክቶች ጋር የተጣበቁ ሁሉም ምስሎች ተለዋጭ መግለጫዎችን ማካተት አለባቸው፡፡

e. **ዋትስ አፕ(WhatsApp)** ተደራሽ ሲሆን ከ ቶክባክ እና ቮይስ ኦቨር ጋር አብሮ ይሰራል። ሲሪ (SIRI) የ ዋትስ አፕ(መልዕክቶችን ጮክ ብላ እና በአዲስ ስልኮች ላይ ታነባለች እንዲሁም በ ሲሪ በኩል መልዕክቶችን መግለጽ ይችላል። WhatsApp'ን በሚጠቀሙበት ጊዜ ኢሞጂን ከመጠቀም ይቆጠቡ።

f. **ኢሜል(E-Mail)፥** COVID-19'ን በተመለከተ የኢሜል ማስታወቂያዎች በብዙ ቋንቋዎች ተደራሽ መሆን አለባቸው፡፡ ሶፍትዌሩ በተለያዩ መሣሪያዎች ላይ እንከን ሳይኖረው እንዲሠራ እንዲሁም ተገልጋዮችን የሚረዳ ቴክኖሎጂ ጋር እንዲሰራ ለማስቻል ሶፍትዌሩ እንደ የተደራሽነት መመሪያዎች መሰረት መቀረጽ አለበት። አንዳንድ የዴስክቶፕ ማሳወቂያ ስርዓቶች መልእክቶችን ከጽሑፍ እና ድምጽ በተጨማሪ በተለያዩ ቅርፀቶች እንደሚላኩ ሚያረጋግጡ ናቸው፡፡
ከ COVID-19 ጋር በተዛመዱ ማንቂያዎች ለይ ግራፊክስ መጠቀም ጽሑፉን የመረዳት ችግር ያለባቸው ሰዎች ሊረዳ ይችላል። ሁሉም ምስሎች አማራጭ መግለጫዎችን ማካተት አለባቸው ፡፡[7]

g. **ማህበራዊ አውታረ መረቦች፥** በጣም ታዋቂዎቹ የማህበራዊ ሚዲያ አውታር መረቦች፣ አዳዲሶቹ ስሪቶች ይበልጥ ተደራሽ እየሆኑ ናቸው። ያማለት ፌስቡክ፣ ኢንስታግራም፣ ትዊተር፣ ዩቲዩብ የተደራሽነት ባህሪያትን ይሰጣሉ ማለት ነው፡፡ ለሁሉም ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስለ COVID-19'ን እና ወረርሽኙ ለይ ሚወሰዱ እርምጃዎችን በነዚህ መረቦችህ ለይ ሚያሰራኡ የህክምና እና የመረጃ ኤጀንሲዎች ስለ ዲጂታል ይዘት ተደራሽነት ማወቅ አለባቸው።[8]

h. **ድህረ ገጽ፥** ዓለም አቀፍ/ክልላዊ ወይም ብሄራዊ ብክለትን ለመቀነስ የ COVID-19 እና ተዛማጅ መረጃዎችን የሚሰጡ ድህረ ገጾች አካል ጉዳተኞች በድር ገጹ ላይ የተጋሩትን አስፈላጊ መረጃዎች በሚመለከቱበት ጊዜ እንቅፋት እንዳይገጥማቸው ቀደም ብለው ተደራሽ መሆናቸውን መፈተሽ አለባቸው፡፡ በድር ጣቢያ በኩል የቀረቡት ሁሉም ተዛማጅ ዲጂታል ሰነዶች (word, PDF) በ እስክሪን አንባቢ (Screan reader) ለሚጠቀሙ ሰዎች ተደራሽ የሆኑ/ተደራሽ ያልሆኑ ሊሆኑ ይችላኡ በድምጸት ሊነበቡ በማይችሉ ቅርጸቶች ከሆኑ፣ እንደ JPEG ፋይሎች ወይም ተደራሽ ያልሆኑ ምስሎች ላይ የተመሰረቱ ፒዲኤፎች (ለምሳሌ እስካን የተደረጉ ምስሎች) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡[9]
በሌላ በኩል፣ ምስሎች እና ግራፊክስዎች የግንዛቤ ችግር ላለባቸው ወይም የቋንቋ ልዩነት ላላቸው ሰዎች ይዘትን ለማሳየት ጥሩ መንገዶች ናቸው፥ ሆኖም ወደ ድምጽ ወይም ወደ ብሬይል ማሳያ የሚቀይር የእስክሪን ማንበብያ ሶፍትዌር የሚጠቀሙ የእይታ እክል ያላቸው ሰዎች መረጃውን ሊቀበሉ እና ሊረዱ መቻላቸውን ለማረጋገጥ እነዚህ ከጽሑፍ መረጃዎች ጋር መደገፍ አለባቸው። ወደ ውጫዊ ድር ገጽዎች የሚወስዱ አገናኞች(links) ገላጭ መሆን አለባቸው። ማውዝ(mouse) ለማይጠቀሙ ሰዎች ሁሉም የድህረ ገጹ አካሎች በቁልፍ ሰሌዳው(keyboard) በኩል ተደራሽ መሆን አለኣቸው።[10]

---

[7] *ማይክሮሶፍት ፥ የ አውትሉክን (Outlook) ኢሜልዎን ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ያድርጉ

[8]*የእንግሊዝ መንግስት ዲጂታል አገልግሎት። ማህበራዊ ሚዲያ ጨዋታ መጽሐፍ(playbook) - ተደራሽነት

[9]*የድር ገጽ ይዘት ተደራሽነት WCAG 2.1 መሆኑን የሚያረጋግጥ መለኪያ

[10] *የ W3C ድር ገጽ ተደራሽነት ተነሳሽነት ትምህርቶች

***የITU ንብረት አይደለም:** በእነዚህ ጣቢያዎች ላይ ያሉ ሁሉም መረጃዎች በቅን ልቦና የቀረቡ ናቸው፣ ሆኖም ምንም ዓይነት ውክልና፣ ማስተዋወቂያ ወይም ዋስትና አንሰጥም፣ የቀረበልን መረጃ ትክክለኛነት፣ አስተማማኝነት፣ ተገኝነት ወይም የተሟላነት በተመለከተ ምንም ዓይነት መግለጫ አንሰጥም ውጫዊ ጣቢያዎች በተመለከተ።

የተለየ ፍላጎቶች ላላቸው ግለሰቦች ዲጂታል አካታችነት ለመደገፍ ተጨማሪ ITU ግብዓቶች እና መረጃዎች እባክዎን የተከተሉትን ይመልከቱ: የተወሰኑ ፍላጎቶች ላላቸው ግለሰቦች ICT ተደራሽነት እና ITU-D ዲጂታል አካታችነት።

---

[i] **እነዚህ መመሪያዎች የማያስለቹ ናቸው**
ለትርጉሙ ሃላፊነት አለመሰድ፡ አጭሩን የ ITU መመሪያዎች በ "ዲጂታል መረጃ፣ አገልግሎቶች እና ምርቶች በ COVID-19 ግዜ አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ፣ ለሁሉም ሰዎች አንዴት ተደራሽ ማድረግ እንደሚቻል ማረጋገጥን በተመለከተ።" ለይን በትከከል ወደ ለላ ቋንቋዎች ለመተርጎም በሚገባ ጥርረት ተደርጓል፣ ከ ኦሪጅናሎቹ 6 የ UN ቋንቋዎች እንግሊዘኛ፣ አረቢኛ፣ ቻይኒኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ራሺኛ እና ስፓኒሽኛ በተቸማሪ። በተጠቀሱት የተወሰኑ ቴክኒካዊ ቋንቋዎች ምክንያት በትንሽ ልዩነት ሊከሰት ይችላል፡፡ ለማንኛውም ስህተቶች ፣ ግድፈቶች ፣ ስለ ጽሑፉ ትክክለኛነት አሻሚነት ፣ ወይም የተተረጎመ መረጃ ለይ አስተማማኝነት አይወሰድበትም። ልዩነት በሚኖርበት ጊዜ የእንግሊዘኛ ኦሪጅናል ሥሪቶች ያሸንፋሉ።